የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ገጽ
የሰበር መ/ቁ 238289

ሰኔ 25 ቀን 2016 ዓ/ም

የወንጀል መዛግብት ሰበር ችሎት

ዳኞች:- ሱልጣን አባተማም

ሽመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

ዓለማየሁ ሹናራ

ተናኘ ጥላሁን

አመልካች:- ወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ አልቀረቡም

ተጠሪዎች፦ 1. ወ/ሮ አፄ ሮባ — አልቀረቡም

2. የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ታህሳስ 4 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 220335 ጥቅምት 01 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው።

ጉዳዩ የጉዳት ካሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ነው። በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ተከሳሽ፤ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፤ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣ/ገብ በመሆን ተከራክረዋል። 1ኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፦ የአሁን አመልካች የ1ኛ ተጠሪ መሬት ስፋቱ 0.5082 የሆነው አዋሳኙ ክሱ ውስጥ የተጠቀሰው የ2005 እና 2008 ዓ/ም ፕሮጀክት ለማስፋፋት የ1ኛ ተጠሪን እርሻ መሬት ጨምሮ ለማልማት ነው የወሰደው፤ ከመሰረቱ ይህ እርሻ መሬት አመልካች ለማልማት ወስዶ አመልካች እና

የወረዳው አስተዳደር የሽግግር ጊዜ ስምምነት በ 2006 ዓ/ም በመቋቋም በመካከላቸው ውል ተመስርቷል፤ አመልካች የእርሻ መሬቴን ለማልማት ብሎ ወስዶ የሸንኮራው አገዳ ተተክሎ ውጤት እስኪሰጥ ለዚህ ላይ ማግኘት ያለበት እህል ስለሚቆም ማቆያ በውሉ መሰረት ሲከፍል ቆይቷል፤ አመልካች ለልማት ብሎ የወሰደውን መሬት ሸንኮራ አገዳውን እንዲያጠፋበት በማለት ቆፍሮ ውሃ በውስጡ በማፍሰስ ገደል አድርጎ አፈሩንም እላው ላይ ከምሮ ከእርሻው አገልግሎት ውጪ ስላደረገው እዚህ መሬት ላይ ማቆያ ሲከፍል ቢቆይም አሁን ማቆያውን ስለአቋረጠብኝ፤ የእርሻ መሬቴን ከእርሻ አገልግሎት ውጪ አድርጎ ወደ በፊቱ ቦታ መመለስ አልቻልንም ስለዚህ አመልካች ቋሚ ካሳ ብር 609,804.00 (ስድስት መቶ ዘጠና ሺህ ስምንት መቶ አራት ብር) በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀጽ 1 (ሐ) እና 2 (ሐ) እና በደንብ ቁጥር 472/2012 አንቀጽ 26 እና 34 (2) በሚያዘው መሰረት እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

አመልካች ለክሱ የሰጠው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር መልስ ይዘት በአጭሩ ይህ የሸንኮራ አገዳ ልማት ማስፋፍያ ፕሮጀክት ከ 2006 ዓ/ም በፊት የተሰራ በመሆኑ የ 1 ኛ ተጠሪ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 መሰረት በሁለት አመት ይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል፤ 1 ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የለውም፤ በመካከላችን ያለው ግንኙነት ውልን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም በሚል ክሱን የተቃወመ ሲሆን፤ በፍሬ ነገር መከራከርያ አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 8(3) በተደነገገው መሰረት የሽግግር ጊዜ ውል ስምምነት በ 2006 ዓ/ም የተደረገው በአዳማ ወረዳ አስተዳደር እና በሸንበሌጥ እና ቦሎ የሸንኮራ አገዳ አምራቾች ሕብረት ስራ ማሕበር የሚባል 1 ኛ ተጠሪ አባል የሆነችበትን ማሕበር ጨምሮ እነዚህ ሶስት አካላት መካከል በተፈረመ የሶስትዮሽ ውል መሰረት መሆኑን፤ የውሉ አላማም በፕሮጀክቱ አካባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮች በማሕበር ተደራጅተው በማሕበራቸው በኩል እንደዋናነት ከእነሱ ጥቅም ጋር ሲሰራ የነበረ ሲሆን አመልካች ፍብሪካ ድርሻ በአርሶ አደሮች ቦታ ሆኖ ይህን ሸንኮራ አገዳ ለማልማት የሚያስፈልጉ ነገሮችን እንደ ውሃ የሚያልፍበት ቦይ፤ ከእርሻ መሬት ውስጥ ጎርፍ የሚወጣበት ቦይ እና ከሌላ ቦታ የሚመጣ የውሃ ጎርፍ መከላከል፤ ሸንኮራው ተጭኖ የሚወጣበት መንገድ እና የመሳሰሉት ነገሮች በማመቻቸት ለማህበሩ ድጋፍ በማድረግ እና ሸንኮራው በሚደርስበት ጊዜም ከማህበሩ ጋር የሽያጭ እና ግዢ ውል በመፈፀም ማህበሩ በአፈሉ ገንዘብ ሸንኮራው የሚገዛ እንጂ ከመሬቱ ላይም ሆነ ከሸንኮራው ምርት ላይ አመልካች የባለይዞታነት መብት የሌለው መሆኑ፤ ተጀምሮ የነበረው የሸንኮራው ልማት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በ 22/8/2010 ዓ/ም የ 1 ኛ ተጠሪን ለልማት ተለይቶ የነበረውን መሬት ለእርሻ እዲመለስለት ተደርጓል፤ ስለዚህ ልማቱ በዚህ መልክ ከአቅም በላይ በሆነው ለቆመው በፍ/ህ/ቁ አንቀጽ 1792 እና 1793 መሰረት ከለደረሰው ጉዳት በአመልካች ፋብሪካ ምክንያት በግሉ የህግ ተጠያቂነት የሚወሰድበት አንድም ነገር ስለሌለ የ 1 ኛ ተጠሪ ክስ መሰረት ሆነ በቂ ማስረጃ የለውም ተብሎ ውድቅ እንዲሆንለት፤ ስለዚህ ቋሚ ካሳ በአመልካች በኩል 1 ኛ ተጠሪ በጠየቀችው መሰረት የሚከፈል የለም፤ ይህን የተባለውን መሬት የቆፈረው የአመልካች ፍብሪካ ሳይሆን የኦሮሚያ ግንባታ ኮሬፖሬሽን ስለሆነ በተሰጠው ዲዛይን መሰረት እና በሰኔ 13/2002 ዓ/ም በመካከላቸው በተፈጸመው ውል መሰረት እና ሙያውን አማካይ በማድረግ ባለመስራቱ የደረሰ ጉዳት ካለ ለደረሰው ጉዳት ሙሉ ተጠያቂነት መውሰድ ያለበት በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሰረት ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባልን በማለት ጠይቋል።

2ኛ ተጠሪም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሰረት ጣ/ገብ ሆኖ ተጠርቶ በሰጠው መልስ የ1ኛ ተጠሪ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባልኟ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የለውምኟ ለሚለው አመልካች የጣ/ገብነት ጥያቄ ያቀረበበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. አንቀጽ 43 መሰረት መስፈርቱን የሚያሟላ አይደለምኟ የጣልቃ ገቡ ድርሻው እና የድርሻው መጠን በግልጽ ተዘርዝሮ ተገቢነት ባለው ማስረጃ ተደግፎ ከአመልካች ላይ የቀረበ አይደለም በማለት እንደ መጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧልኟ አመልካች እና ጣ/ገቡ መካከል የፕሮጀክት ግንባታ ማስፍፊያ የወለንጪቲ ሸንኮራ ልማት በሰኔ 13/2002 ዓ/ም በተደረገ (ዋናው ውል) እና ልዩ ውል ስምምነት ግንባታ 2005 ዓ/ም የተደረጉ አለኟ የጎርፍ መከላከያ ቦይ ግንባታ እዚህ ክርክር ያነሳው መሬት ላይ ደረሰ የተባለው ጉዳት ይህ ምክንያት የሆነው የተሰራው በግንቦት ወር 2005 ዓ/ም በተደረገው ውል ስምምነት መሰረት አማካሪው ኢንጂነር የባቶ ደጋጋ አርሶ አደር ቀበሌ ውስጥ ይህ አሁን ክርክር ያስነሳው መሬት ጨምሮ የጎርፍ መከላከያ ስራ እንዲሰራ ትዕዛዝ ስለሰጠ ጣልቃ ገቡም ባለው ውል መሰረት አመልካች አዋስኖ የሰጠው መሬት ላይ በዲዛይኑ እና በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የአማካሪ ኢንጂነር ክትትል እና ቁጥጥር ባለቤት ቦታ ካለአንድ ጥፋት የስራ ስለሆነ ያለበት ተጠያቂነት የለምኟ ስለዚህ ጣ/ገቡ ስራውን በዲዛይን እና በውል መሰረት ካለ አንድ ጥፍት እሰከሰራ ድረስ ተጠያቂነት የለበትም ተብሎ በነጻ እንድሰናበት በማለት ጠይቋል።

ጉዳዩ በዚህ አግባብ የቀረበለት ፍ/ቤትም የመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦችን በብይን በማለፍ በፍሬ ጉዳይ ረገድ ክሱን ሰምቶ እንዲሁም የጉዳቱን አይነት እና መጠን በሚመለከተው የመንግስት አካላት ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃውን መርምሮ 2ኛ ተጠሪ (የስር ጣ/ገብ) አመልካች (የስር ተከሳሽ) ባዘጋጀው ዲዛይን መሰረት ተወስኖ በተሰጠው መሬት ላይ ግራቀኙ ባደረጉት ውል ስምምነት መሰረት ስራውን የሰራ መሆኑን በአማካሪ ድርጅት በነበረው የኢትዮጵያ ዲዛይን ስራዎች ቁጥጥር ውሃ እና ኢነርጂ በኩል የቀረበው ማስረጃ የሚያረጋግጥ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ (የስር ጣ/ገብ) ከተሰጠው ዲዛይን ውጪ መስራቱ ስላልተረጋገጠ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑንኟ ፍርድ ቤቱ በባለሙያዎች እና ጉዳዩ በሚመለከታቸው የተለያዩ የመንግስት መዋቅር በምስራቅ ሸዋ ዞን አስተዳደር ሰብሳቢነት የአዳማ ወረዳ የመሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ጽ/ቤት ባለሙያዎች የግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት የገበያ ልማት ጽ/ቤት እና ባቶ ደጋጋ ገ/ማህበር ቀበሌ አስተዳደር ተወካዮች በተገኙበት እንዲጣራ በማድረግ በቀረበው ሪፖርት የ1ኛ ተጠሪ መሬት አፈር እላዩ ላይ በመከመሩ ምክንያት ለምርት ሊውል የሚችል የለማ አፈር በመቀበሩ የአፈር መዋቅሩ የተረበሸ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የጎርፍ ቦይ በውስጡ በመውጣቱ ተመልሶ የማይጠገን ገደል ሆኖ በጣም መሬቱ ስለተበላሸ መሬቱ ወደ ነበረበት ተመልሶ ምርት ሊሰጥ የማይችል መሆኑን ይህን ድርጊት እንዲፈጽም ያደረገው አመልካች (የስር ተከሳሽ) መሆኑን መረጋገጡን ገልጾ አመልካችን (የስር ተከሳሽን) ለክሱ ኃላፊ በማድረግ የ1ኛ ተጠሪ (የስር ከሳሽ) እርሻ መሬት ከጥቅም ውጪ የሆነው ስፋቱ 0.52 ሄክታር መሆኑን ሲያመርትበት የነበረው በቆሎ እንደሆነ መረጋገጡን ጠቅሶኟ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 መሰረት የ15 ዓመት በቆሎ ምርት ብር 655020 መሆኑ መረጋገጡ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ (የስር ከሳሽ) ከጠየቁት ዳኝነት በላይ ሊወሰን ስለማይችል በጠየቁት ዳኝነት መሰረት ብር 609804 (ስድስት መቶ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ አራት ብር) ወጪና ኪሳራ ጨምሮ አመልካች (የስር ተከሳሽ) ለ1ኛ ተጠሪ (ለስር ከሳሽ) እንዲከፍል በማለት ወስኗል።

አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱም የይግባኝ ቅሬታውን መርምሮ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348 (1) መሰረት በአብላጫ ድምጽ አጽንቶታል።

አመልካች ታህሳስ 4 ቀን 2015 ዓ/ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- በመጀመሪያ ደረጃ የተነሳውን የፀርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገው አለአግባብ ስለመሆኑ፤ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የሌለው መሆኑን፤ ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት ለ1ኛ ተጠሪ ጥቅም ሲባል በውላችን አንቀጽ 2፣8 እና 9 መሰረት በብድር የተዘረጉ መሰረተ ልማቶች በውል ዘመኑ ውስጥ ነው ስለዚህ ይህ በውል የፈጠርነው መብት እና ግዴታዎች በዋናነት መገዛት ያለበት በፍ/ብሔር ህጉ ስለ ውል በጠቅላላው 1676 (1)፣1731፣1763 እና 1771 ውሎን ያፈረሰ ወይም ግዴታውን የልፈፀመው ማን እንደሆነ ካለው ፍ/ብሔር ህግ፣በውላችን (አንቀፅ 1፣10-13) እና ማስረጃ ጋር ሳይጣራ በዚህ ጉዳይ ላይ አግባብነት የሌለው ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት ካሳየሚከፈልበት እና ተነሽዎች መልሶ የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1161/2011 መሰረት የ15 ዓመት መፈናቀያ ካሳ ክፍያ እንድንፈጽም በስር ፍ/ቤት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለተፈጸመብን እንዲታረምልን፤ ለክርክር ምክንያት የሆነው መሬት ላይ አመልካች እና ተጠሪዎች የምንገዛበት በመካከላችን በጽሑፍ የተደረገ የውል ስምምነት አለን፤ ይህ በመካከላችን የነበረው ውል ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ተቋርጧል፤ በዚሁ ውላችን አንቀጽ 11 (3) (ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በዚህ ውል የገባውን ግዴታ መፈጸም ያልቻለ ወገን ከኃላፊነት ነፃ ነው) የሚለውንም በግልጽ ቀደም ብለን ተስማምተናልና ከ9 ዓመት ወደኃላ ተመልሰን ወይም ጉዳዩን ወደ አዋጅ 1161/2011 በመለወጥ ኃላፊ የምንሆንበት የህግ እና የውል መሰረት የለውም እንዲባልልን እና በስር ፍርድ ቤቶች በየደረጃው የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አጠቃላይ ክርክሩንና የፀርጋውን መከራከሪያ ጨምሮ በውል ህግ ተመስርቶ ከተመረመረ የካሳው ስሌት በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 መሰረት የመሰላቱን አግባብ ለማጣራት የሚል ጭብጥ ይዞ በማስቀረቡ ግራ ቀኙ ክርክር አድርገዉበታል።

1ኛ ተጠሪም የካቲት 14 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ለአንድ አርሶ አደር እና ለሚያስተዳድረው ቤተሰቡ የእርሻ መሬቱ የህልውናው መሠረት፤ የመኖር እና ያለመኖር ጉዳይ ሲሆን አመልካች ይህንን የ1ኛ ተጠሪ እና 1ኛ ተጠሪ የሚያስተዳድረውን ቤተሰብ ህልውና የሆነውን ይዞታዬን አለማልሃለሁ በሚል ምክንያት ተቀብሎኝ ዳግም ለዘላለም ለእርሻ ስራ እንዳይውል በማድረግ የእኔን እና የቤተሰቤን ሕይወት አጨልሞ ውል አቋርጦ በጥፋቱ ላደረሰው ጉዳት ካሳ እንዲከፍል ሲወሰንበት ውሳኔው አግባብነት የለውም፤ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረትዊ የህግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው በማለት የህግ ድንጋጌዎችን ለእርሱ በሚረዳው መልኩ በማጣመም ያለአግባብ ያቀረበ በመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት ጉዳዩን በጥሞና ተመልክቶልኝ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረትዊ የህግ ስሕተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት እንዲያጠናዉ እጠይቃለሁ የሚል ነዉ ።።

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ የካቲት 13 ቀን 2015 ዓ/ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በነበረው የስራ ተቋራጭ ውል መሰረት የአመልካቿን የፕሮጀክት ሥራ በተሰጠኝ ዲዛይን መሰረት በአግባቡ ከመስራት ውጪ በራሱ ፍላጎት

ወይም ከዲዛይን ውጪ በመስራት በ 1 ኛ ተጠሪ መሬት ላይ ያደረሰው ጉዳት ስለሌለ ተጠያቂነት የለበትም ተብሎ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል ብሏል።

የሰበር አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ ክርክሩ በዚሁ ተጠቃሏል። እኛም ቅሬታዉ ያሥቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ ፤በስር ፍርድ ቤት ከተደረገዉ ክርክር ፤የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሰኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል። አንደመረመረዉም የሰበር አጣሪ ችሎቱ የያዘዉ ጭብጥ አጠቃላይ ክርክሩንና የይርጋውን መከራከሪያ ጨምሮ በውል ህግ ተመስርቶ ከተመረመረ የካሳው ስሌት በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 መሰረት የመሰላቱን አግባብነት ለማጣራት በሚል ሲሆን አመልካች ለክሱ ሃላፊ የተደረገዉ የውሃ ጎርፍ ከላይ ፈሶ ሸንኮራ አገዳ ውስጥ የሚተኛውን ዉሃ ለመከላከል ብሎ በሁለተኛዉ ተጠሪ ቦይ ሲያሰራ ክርክር ያስነሳዉን የአንደኛ ተጠሪ መሬት ቁልቁል ቆፍሮ ገደል በማድረግ አፈሩን ጠርጎ ከጎኑ መንገድ ላይ አውጥቶ ገረጋንቲ አፈር እላዩ ላይ በማድረግ በቋሚነት ከእርሻ አገልግሎት ውጪ አድርጓል ተብሎ ነዉ።

የአንደኛ የሰበር ተጠሪ የመሬት ይዞታቸዉ በአመልካች ጥፋት ምክንያት በቋሚነት ለእርሻ ስራ ጥቅም ላይ ሊዉል እንዳይችል የተደረገ መሆኑ፤በ 2 ኛ ተጠሪ በኩል ከአመልካች ጋር በነበረው የስራ ተቋራጭ ውል መሰረት የአመልካቹን የፕሮጀክት ሥራ በተሰጠዉ ዲዛይን እና ዉል መሰረት በአግባቡ የሰራ መሆኑን እና እና ከዲዛይን ውጪ በመስራት በ 1 ኛ ተጠሪ መሬት ላይ ያደረሰው ጉዳት የሌለ መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸዉ በታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ መሆኑን የተረዳን ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ ለደረሰዉ ጉዳት ሃላፊነት የለበትም መባሉ ተገቢነት ያለዉ ነዉ ብለናል። የሰበር አመልካች የአንደኛ ተጠሪን የካሳ ክፍያ ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 ድንጋጌዎች መሰረት ስሌቱ ተሰልቶ ይከፈል የመባሉን አግባብነት በተመለከተ እንደሚከተለዉ መርምረነዋል። የአንደኛ ተጠሪ መሬት በሰበር አመልካች ድርጊት ለዘለቄታዉ ከጥቅም ዉጭ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አንደኛ ተጠሪ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(7) እና (8) እና እነዚህን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ ተከትሎ የወጣዉን አዋጅ ቁጥር 1161/2011 መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2027 እና 2035 ድንጋጌዎች መሰረት ካሳ እንዲከፈላቸዉ ዳኝነት የማይጠይቁበት የህግ ምክንያት የለም። በአመልካች እና በሁለተኛ ተጠሪ መካከል ያለዉ ዉል ደግሞ በአመልካች ላይ ግዴታ የሚጥል በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1731 መሰረት ሃላፊነቱ የአመልካች ከመሆኑም በላይ ሁለተኛዉ ተጠሪ ከዉሉ ይዘት ዉጭ ይዞታዉን የተጠቀመ መሆኑን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ሳያረጋግጥ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚያቀርበዉ ክርክር የህግም ሆነ የማስረጃ ድጋፍ ያለዉ አይደለም።

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች በአሁን አመልካች ጥፋት ምክንያት ዘላቂ ጉዳት ጉዳት የደረሰ መሆኑን አረጋግጠዉ የጉዳት ካሳ ክፍያ ስሌቱን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 ለህዝብ ጥቅም ሲባል ይዞታ የሚለቀቅበት እና ለንብረት ካሳ ሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ መሰረት አስልተዉ ለአሁን የሰበር አንደኛ ተጠሪ ካሳ መወሰናቸዉ በአንደኛ ተጠሪ መሬት ላይ የደረሰዉ ጉዳት ዘላቂ ጉዳት ከመሆኑ አንጻር ለደረሰዉ ዘላቂ ጉዳት ተመዛዛኝ የሆነዉን ካሳ ለመወሰን በሚያስችል ሁኔታ ዉሳኔ መሰጠታቸዉን የሚያሳይ በመሆኑ እና የጉዳት ስሌቱ ስለ ዉል በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ሊሰላ የሚችልበት የተሻለ ሁኔታ ስለሌለ እንዲሁም ለዚህ ጉዳይም በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ልዩ ህጎች ስለሆኑ ስሌቱ በዚህ አዋጅ መሰረት መሰላቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ሊባል የሚችል አይደለም። በሌላ በኩል በዚሁ

ተመሳሳይ ጉዳይ ከዚህ በፊት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 139432 እና በሰ/መ/ቁ 135184 ላይ የህንን ዓይነት ተመሳሳይ ጉዳት ለደረሰባቸዉ ሰዎች ካሳ ሲወሰን የጉዳት መጠን ስሌቱ በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ አዋጅ ቁጥር 455/97 መሰረት ሊሰላ እንደሚገባዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት ስለሆነ እና አዋጅ ቁጥር 455/97 ን አሁን ተክቶ ስራ ላይ ያለዉ ተመሳሳይ አዋጅ ደግሞ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 ስለሆነ ለዚህ ጉዳይም ተፈጻሚነት ያለዉ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 መሰረት በሰበር አንደኛ ተጠሪ የእርሻ መሬት ይዞታ ላይ ለደረሰዉ ዘላቂ የጉዳት ካሳ መጠን ተሰልቶ የተሰጠዉ የጉዳት ካሳ ክፍያ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻል አይደለም።

በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

ዉሳኔ

በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቀ/ 338712 በ 17/03/2014 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 220335 ጥቅምት 01 ቀን 2015 ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348 (1) መሰረት ጸንቷል።

የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪ ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ።

በዚህ ችሎት ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል። ለሚመለከተዉ ክፍል ይጻፍ ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ት